# በፀረ ሙስና ትግሉ ላይ ለምትሰጡት አፍራሽ አስተያየት መስሚያችን ጥጥ ነው

ዮናስ 05/24/13

ሃገራችን ለተያያዘችው ሰፊ የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅድ መሳካት ህገመንገስታችን በራሱ ምቹና አስተማማኝ ስለመሆኑ ብዙዎቹ ይስማማሉ። በመንግስት በኩል በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ከሆነም አገራችን ካለችበት አስከፊ የሆነ ድህነት መውጣት የምትችለውና በዚሁ የትግል ሂደት ላይ የመገኘት ሚስጢርም ይኸው የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና  ህዝቦች አምነውና ፈቅደው ያፀደቁት ህገመንገስት ነው።

ነገር ግን ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ሃገሪቱ የተያያዘችው የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አንዳንዴ ባለበት አልፎ አልፎም ጉዞው የኋልዮሽ የሆነ ስለመምጣቱ የሚናገሩ አስተያየት ሰጪዎች ከሚያስቀምጧቸው ምክንያቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቅሱት ሙስናን ነው። ህገመንግስታችን ወርቅ ነበር በማለት አስተያየታቸውን የሚያጠናክሩት ግለሰቦች በሙስና ምክንያት የህግ የበላይነት እየረከሰ ነው፤ ጥቅማጥቅምና ገንዘብም የህግ የበላይነትን ስፍራ ወርሰው ህገመንግስቱን አደጋ ላይ እየጣሉት ነው ይላሉ። አስቸኳይና ፈጣን እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ በሴሚናርና በመገናኛ ብዙሀን ላይ ስለፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎች በመለፈፍ የሚመጣ አንዳች ነገር ሊኖር እንደማይችል አስተያየት ሲሰጡ የነበሩ ግለሰቦች አደጋውን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመኑ የተያዙ ሰፋፊ ስራዎች ለሙስና መጋለጣቸው አይቀሬ በመሆኑ ነው ይላሉ።

በርካታ የልማት ድሎች በተመዘገቡበት በዚህ ሰዓት በርካታ የመሰረተ ልማት አውታሮች በከተማና በገጠር በመገንባት ላይ ይገኛሉ። በርካታ የሃይል ማመንጫዎችን በአለም ላይ ባልተደረገ ሁኔታ በጥቂት እና በተከታታይ አመታት መገንባታችንም እሙን  ነው። ዓባይን ለልማት የሚያውልና የብዙዎች ቁጭት ከነበረው ውሃ መቋደስ የሚያስችለን ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብንም በመስራት ላይ እንገኛለን። ሊያውም እኛው መሃንዲስ እኛው ግንበኛና እኛው መቀነታችንን ፈትተን። ነገር ግን እነዚህን የመሳሰሉና ከደሃ መቀነት ላይ ጭምር ተቆንጥሮ  በመሰራት ላይ የሚገኙ  የፕሮጀክት ግዢዎች ለሙስና ከተጋለጡ ማታ በቴሌቭዥን  ሙስናን የሚዋጉና  ቀን ደግሞ ከሙስና ጋር ሲዳሩ  ለሚውሉ መንታፊና ሞላጫ ባለስልጣኖች እንዲሁ የምንተወው ከሆነ የሃገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ መገመት ከባድ አይሆንም።

በርካታ ኢንቨስተሮች ከአውሮፓና ከመካከለኛው ምስራቅ ወደሃገራችን እየገቡ ነው፤ ከዚህ በላይ ኢንቨስተሮች እንዲገቡም መንግስታችን የዲፕሎማሲውን መስክ በአዲስ መልክ በማዋቀርና ልኡካኑን በመላክ እየተለማመነ ነው። ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎችም እየታዩ ነው። ነገር ግን በዚህ ሂደት ውስጥ ሃላፊነት ያለባቸው ሰዎች በሙስና የሚጨማለቁ ከሆነ ኪሳራው ብዙ አይነት ነው። የገፅታ እና የስነ ልቦና ኪሳራው ደግሞ ከሁሉም ይከፋል፤ ዜጎች ተስፋ ይቆርጣሉ፤ ውንብድናና ስርዓት አልበኝነትም ይነግሳል።

ሙስና የትም ሊፈፀም ይችላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ሙሰና መፈፀም ግን የዚህችን ሃገር የልማት ቅስም መስበር ነው። የዜጎችን ተስፋም ማኮላሸት ነው። በዚህች ሃገር የሚፈፀም ሙስና፣ ለታላላቅ ፕሮጀክቶቻችን ከህጻናት ተማሪዎች ጀምሮ ቦንድ በመግዛት የዜግነት ድርሻቸውን በመወጣት ላይ በሚገኙት ሁሉ መቀለድ ነው። ሊያውም በያይነቱ መብላት የተሳነው ዜጋ ባለበት ሃገር ላይ በያይነቱ በሆነ ብር ላይ ብር ለብሶ እና ብር ተንተርሶ የሚተኛ ባለስልጣን ነቀዝነት ደም መጣጭነት እና ፊጋነት ቢሆን እንጂ ምን ሊሆን ይችላል።

የዛሬው ጉዳዬም ይኸው ነው። ብር አንጥፈው ብር ተንተርሰውና ብር ለብሰው የተገኙ ባለስልጣናት ላይ ከሰሞኑ የተወሰደውን እርምጃ ተከተሎ ለወትሮው መጥፎ አሰራሮች ይወገዱልን፤ መልካም አስተዳደር ይስፈንልን ፍትህ ይንገስ፣ የህግ የበላይነት ይረጋገጥ፣ ወንጀለኞች ይጥፉ፤ ሙሰኞች ይወገዱ ሲሉ የነበሩ ግለሰቦች፤ ጣታቸውን በመንግስት ላይ ሲቀስሩ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በርግጥም ሙስና የልማታችን ጠንቅ፤ የማንነታችን ነቀርሳና ካንሰር እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲገልጽ የከረመው መንግስት ሙሰና ከወርክሾፕና ከመገናኛ ብዙሃን በዘለለ በተግባር መወገድ ስላለበት ላለፉት ዓመታት ሲያከናውን የነበረውን ጥናትና መረጃ የማሰባሰብ ስራ በማጠናቀቅ ይኸው አንደኛውን እርምጃ የሙስና ስስ ቦታ በሆነውና ተጋላጭነቱ ከሁሉም ተቋማት በከፋው የገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ሲጀምር ከላይ ከተጠቀሱቱ ሃይሎች የማይመስሉና የማይመጥኑ እንዲሁም የተለመዱና ህዝብን ከገዛ ጥቅሙ ጋር ሊያጋጩ የሚችሉ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው።

ስለሆነም መንግስት ለዜጎች ያቀረበው የፀረ ሙስና ትግሉ ጥሪ መጀመር ያለበት የእነዚህን ግለሰቦች አስተያየት በመድፈቅና ማንነታቸውን በማጋለጥ እንዲሁም የሙሰኞቹ ግብረ አበሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ በመጠርጠርና ርካሽ ለሆነ የፖለቲካ ትርፋቸው እጅ ባለመስጠት መሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።

በዚሁ መሰረት በአዲስ ጉዳይ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 164 ግንቦት 2005 ልዩ እትም ላይ የወጡ የፀረ ሙስና ትግሉ ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ አስተያየቶችን እና ሊበረታቱና ቀጥሉበት የሚያሰኙ አስተያየቶችን በማንሳት ምክንያታዊ የሆነ የአፀፋ ምላሽ እሰጣለሁ። ምክነያቱም ዜጋ ነኝ። ከእኔም

ኪስ፤ ከእኔም ደሞዝ ላይ ሰዎቹ ከልጆቹ ጉሮሮ በተነጠቀ ብር ላይ ተኝተው፤ አባቴ የከፈለውን ግብር ተንተርሰው እና እናቴ ከችርቻሮ ሱቅ ላይ የገበረችውን ለብሰው አይቻችኋለውና።

አዲስ ጉዳይ መጽሔት ሰሞኑን የፌዴራሉ የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮምሽን በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ከፍተኛ ባለስልጣናትና ግብረ አበሮቻቸው ላይ የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ አስተያየት እንዲሰጡት የጋበዛው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ከአንድነት ፓርቲ፣ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያምን በግል፤ ኢ/ር ይልቃል ጌታቸውን ከሰማያዊ ፓርቲ፣ ፕ/ር በየነጴጥሮስን ከመድረክ፣ ዶ/ር ያዕቆብ ሃ/ማርያምን በግል፣ ዶ/ር መራራ ጉዲናን ከመድረክ እና የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉን ከአንድነት ፓርቲ ነው።

ለእዚህ በግልና በፓርቲያቸው ስም ለአዲስ ጉዳይ አስተያየት የሰጡ ግለሰቦች አዲስ ጉዳይ ተመሳሳይ የሆኑ ሶስት ጥያቄዎች አቅርቦላቸዋል። |መንግስት በሙሰኞች ላይ የወሰደውን እርምጃ እንዴት ይመለከቱታል? አንዳንዶች "እርምጃው ከፖለቲካ ልዩነት የመነጨ እንጂ ሙስና አይመስለንም" ይላሉ የእርስዎ አስተያየት ምንድ ነው?" ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ህልፈት በኋላ እንዲህ አይነት እርምጃዎች መወሰዳቸው ኢህአዴግን ቆራጥ አቋም ይዟል ያስብለዋል?´ የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው የቀረቡላቸው።

ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሲምልሱ በኢህአዴግ ውስጥ በፊት ያልነበረና አሁን የመጣ መጥፎ አመለካከት አለ ይኸውም የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ነው። በማለት በፓርቲው ውስጥ ሙስና መንሰራፋቱን ገልፀው የተወሰደውን እርምጃ የላይ ላይና ምናልባትም ከፖለቲካ ልዩነት የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ግምት ያላቸው መሆኑን ይጠቅሱና እርምጃው በራሱ አስፈላጊና ትክክለኛ ቢሆንም የኢህአዴግን ቆራጥነት አያመለክትም ይላሉ።

ፕ/ር መስፍን ደግሞ በተመሳሳይ ለቀረበላቸው ጥያቄ እርምጃው በትክክል በተለይም ከዚህ ቀደም እንደስዬ ያሉ ሰዎች ላይ እንደተወሰደው እርምጃ አለመሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል በማለት እነ አቶ ስዬ ላይ ተወስዶ የነበረው እርምጃ ከፖለቲካ ልዩነት የመነጨ መሆኑን በመደምደም ይህኛውም እርምጃ እንደዚያው ሊሆን ይችላል አይነት አገቦ የተቀላቀለ አስተያየት የሰጡ ሲሆን ታምራት ላይኔን በማስታወስ ጠቅላይ ሚኒስትርም እኮ ታስሮ ያውቃልና የሰሞኑን እርምጃ ከኢህአዴግ ቁረጠኝነት ጋር ማያያዝ ተገቢ አይደለም ብለዋል።

“ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ” አይነት ከተጠየቁት ጥያቄ ጋር ተያያዥ ያልሆነና ልክ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ህወሃትና ብአዴን መበላላት ስልጀመሩ ነው አይነት አስተያየት እርምጃው በስርአቱ ውስጥ የተከሰቱ ምልክቶችን ለማከም ነው የተወሰደ ነው ብለው ስላልተጠየቁት የሃይማኖት የትምህርት ስርአት የመሳሰሉት ጉዳዮች አውርተው ስርአቱ መበላላት መጀመሩን እርምጃው አመላክቷል ይላሉ።

ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ደግሞ ብዙ ጊዜ በፓርቲያቸው ሰዎች የሚታሙበትን ወጣቶችን አለማብቃት ወቀሳ ባለስልጣናቱ ጎረምሳ በመሆናቸው የተከሰተና ቀድሞም ቢሆን ይህ እንደሚሆን ነበረበት ያሉ ሲሆን በውጭ ሃገር የቦርድ አባል የሆነ የኢህአዴግ ባለ ስልጣን አውቃለሁ ስለሆነም እርምጃው የስርአቱን ቁርጠኝነት አያመላክትም ብለዋል።

ዶ/ር ያእቆብ ሃ/ማርያም ደግሞ ሰዎቹ የታሰሩት ከፖለቲካ ልዩነታቸው ጋር በተያያዘ ከሆነ በጣም አሳሳቢ ነው ብለው ካልሆነ ግን እርምጃው የሚበረታታና ግን ደግሞ የስርአቱን ቁርጠኝነት የማያሳይ እንደሆነ ገልጸዋል።

ዶ/ር መራራ በተለይ በኢትዮጲያ ውስጥ ከፖለቲካዊ ውጪ ምንም አይነት የተለየ እርምጃ እየጠፋ ነው በማለት እርምጃውን እንደሚጠራጠሩት እና ይልቁንም የፖለቲካ ልዩነት ሊሆን እንደሚችል በዘወርዋራ ተናግረዋል።

የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ከሰጡት አስተያየት በአብዛኛው የምስማማ በመሆኑና በተለይም የህዝብ ውክልና ካለው ሰው እንዲህ አይነት ሃላፊነት የተሞላበት አስተያየት የሚጠበቅ በመሆኑ የአቶ ግርማን ሃሳብ ከራሴ ማጠቃለያ ጋር ወደኋላ የምመለከተው ይሆንና ከላይ ወደተወረወሩት አስተያየቶች ፍተሻ ልመለስ።

ዶ/ር ነጋሶ እራሳቸውን ለማውጣት በመፈለግ ይመስላል ሙስና እሣቸው የኢህአዴግ አካል በነበሩበትወቅት በሥርዓቱ ውስጥ እንደሌለ በመናገር የሠጡት አስተያየት ግምት ውስጥ የሚጥላቸው ነው፡፡ ኢህአዴግ እሳቸው በነበሩበትና እሣቸውን ያካተተ  ተሃድሶ ያደረገው እሣቸውን ጨምሮ ሥርዓቱ በመበሥበሱ እንደሆነ እሣቸውም በወቅቱ ነግረውናል፡፡

አንድ ሥርዓት እንደ ሥርዓትና እንደ መሪ ድርጅት ከሥህተቱ መታረሙ እንጂ የሚያስመሠግነው ድርቅናማ የሚያስረግመው እንደሆነ ይታወቃል። ከዚያም በላይ እራሡንም በልቶ እንዲጨረስ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ኢህአዴግ ከሥህተቱ በመማር ባህሉ እንደመታወቂ ውስጡ ሥር የሰደደው ሙስና ከህዝብ አልፎ እራሡንም ሊውጠው እንደሚችል በመገንዘብ እርምጃ መወሠዱ ቁርጠኝነቱን እና መታደሡን የሚያመላክት ሲሆን ለእነ ዶ/ር ነጋሦ ደግሞ የኢህአዴግ መታደስና ቁርጥ አቋም መያዝ የጠማቸውን ሥልጣን የውሃ ሽታ አድርጎ እንኳን ሥልጣን ህዝብን ለማገልገል እንደሆነ ቢያውቁትም ህዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ደሙን የመጠጡት ግለሰቦች ሲያዙ ለሚናፍቁት ሥልጣን ሲሉ  እርምጃውን ማንኳሠሥ ሌላ ደባና የባሠ ሙስና ቢሆን እንጂ ሌላማ ምን ሊሆን ይችላል፡፡

ፕ/ር መስፍንም ቢሆኑ የተጠየቁትን ጥያቄ ተንተርሠው እርምጃው የፖለቲካ ልዩነት ይሆን ወይ በሚለው ላይ ሌላ ጠቃሚና ለህዝብ የሚሆነውን ነገር ከመናገር ይልቅ ተጨማሪ የፖለቲካ ቁማር

ለመጫወት ይሞክራሉ፡፡ እነ ስዬም በፖለቲካ ልዩነት ነው የታሠሩት በማለት እነዚህም በፖለቲካ ልዩነት እንጂ በሌላ አይደለም ዓይነት እንድምታ ያለው አስተያየታቸው ውሃ የማይቋጥርና እነ ሥዬ የበሉትንና ያስበሉትን ለምናውቀው ሠዎች ባይነግሩን ይሻላል፡፡

የኢንጂነር ይልቃል አስተያየት ደግሞ  ገና ከመነሻው ቀደም ብዬም እንደገለፅኩት ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ የሆነና ነገር ግን ምን ያህል በጥላቻ ፖለቲካ እንደተሞሉና ስርዓቱ ያደረጋቸውን ማናቸውም በጎ ጎኖች ላለመመስከር የቆረቡ እንደሆነ የሚያረጋግጥባቸውን አስተያየት ነው የሠጡት፡፡

ወደ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ አስተያየት ስመለሥ አስተያየታቸው ያው በሊዝ አዋጁ፣ በውጭ ኢንቨስትመንትና በሠፋፊ የእርሻ ልማት ሥራዎች ላይ የለመድናቸውን የነቀራ አስተያየት ሲሆን የሰጡት ከበሁሉ በላይና ለህዝብ ጥቅም የቆምኩ ነን ከሚል አካል አሉባልታ መስማታችን ግን ያሣዝናል፡፡

በሌላ በኩል አንድ የኢህአዴግ ባለሥልጣን ሡዳን ሃገር  ትልቅ የግል ድርጅት ውስጥ የቦርድ አባል ሆኖ መሰብሰቡን የቅርቤ የምለው ሠው አይቶት ነግሮኛል በማት ስሙንም ላለማንሣት ከመወሠን ይልቅ የህዝብ ነን እንደሚሉን ሁሉ ማስረጃ ሠብስበው ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ማስቀጣትን ነበር ከሣቸው የምንሻው፡፡ ይህን ባለማድረጋቸው እና ስሙን ላለመግለፅ በመወሠናቸው ደግሞ ፕ/ር በየነ ወይ ዋሽተዋል ማንም አልነገራቸውም፣ ካልሆነ ደግሞ እሣቸውም የሙሠኞች አጋር እና ተቆርቋሪነት የሌላቸው ናቸው ብለን እንድንገነዘብ ያስገድደናል፡፡ በተጨማሪም እሣቸውም የቅርብ ሠው ላሉት ዘመዳቸው ምቾት ሲሉ የህዝብን ጥቅም አሣልፈው የሰጡና ስልጣን ላይ ቢወጡም በፖለቲካ ልዩነትና በዝምድና እንጂ በመርህ ሊመሩ የማይችሉ መሆናቸውን አስተያየታቸው ያሳብቃል፡፡

የዶ/ር ያዕቆብና የዶ/ር መራራ ጉዲና አስተያየት በተለይም እርምጃውን ከፖለቲካ ልዩነት ጋር ላያያዙትና ለሚያያይዙት ሁሉ የተከበሩ አቶ ግርማ ሠይፉ አስተያየት በቂ ምላሽ የሚሆን ይመስለኛል፡፡

"እነዚህ ሰዎች የፖለቲካ ልዩነት ቢኖራቸው እንኳን ልዩነታቸውን ማስመዝገብ ያለባቸው በሙስና ከተዘፈቁ በኋላ መሆን የለበትም፡፡ በተለይ የፖለቲካ ልዩነታቸውን  አስቀድመው ማስመዝገብ እንጂ በሙስና ከተጠረጠሩ በኋላ መሆን የለበትም፡፡ በተለይ የፖለቲካ ልዩነታቸውን አስቀድሞ ማስመዝገብ እንጂ በውስጥ ከተጠረጠሩ በኋላ ልዩነት ማስመዝገቡ የሚፈይደው ጉዳይ የለም፡፡ ሌላው እዚህ ጋር ሳይነሣ መታለፍ የሌለበት ነጥብ የተለያየን የፖለቲካ ሃሣብ ማንፀባረቅ የፈለገ ሠው እጅ ከሙስና የፀዳ መሆን አለበት----ጉዳዩን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት ጋር በማያያዝ

ማወሣሠቡንም አልደገፈውም፡፡" ይላሉ፡፡ የእኔም ሃሳብ ይኸው ነው፡፡ የፖለቲካ ልዩነትን ማስመዝገብ አስቀድሞ እንጂ ከተያዙ በኋላ መሆን የለበትም፡፡ ትራስ የሆነው ብራችን፣ አንሶላ የሆነው ዶላራችን ፍራሽ የሆነው ፓውንዳችን እንዲህ ባሉ ተልካሻ አስተያየቶችና የፖለቲካ ልዩነት እንቶ ፈንቶ የሚካሥ አይደለም፡፡ ይልቁንም እንደ ዜጋ ከሃገራችን ሃብት እኩል ተጠቃሚ የሚያደርገንን የህግ የበላይነትን በማስከበር የነፃነት እና የልማት ተሥፋ የሚሞላንን ከእድገቱም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንጂ ቀጥተኛ ከሣሪ የሚያደርገንን እንቶ ፈንቶ የምንሠማበት ጆሮ የለንም፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት እና መኖር ጋር በማያያዝ አስተያየት የሰጡቱ "ምናልባት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከለላ ሰጥተዋቸው ነበር" በማለት ቢዶልቱም የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉም እንዳሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተቃራኒው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መስሪያ ቤትን "የተጨማለቀ መስሪያ ቤት" ብለውት እንደነበር አንዘነጋም ፡፡

የፖለቲካ ልዩነት እስኪወጣ ከመጠበቅ ምነው ታዲያ የተጨማለቀ መሥሪያ ቤት መሆኑ የተነገራቸው ጊዜ መሥሪያ ቤቱን ሠዎቹ ያለቀቁት? ለማያውቁሽ ታጠኝ እንዲሉ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆን ፖለቲካውንም ዲስኩሩንም ቀድሞ በልቶታልና በእናንተ የፖለቲካ ቱማታ ጠግቦ የሚያድር ሆድ የሌለው ህዝብ ትግሉ እንጀራውን ከአፉ ላይ ከነጠቁት እና በማስነጠቅ ሂደት ውስጥ ካሉት ጋር ይሆናል፡፡

በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ለሙሰኞች እንኳንስ ከለላ ሊሆኑ ይቅር እና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በነበሩበት ሠአትና በሣቸው አመራር ሰጪነት ጥናቱ ተደርጎ እርምጃው እንደተወሠደ የኮምሽኑ ኮሚሽነር የተናገሩ ሲሆን ጥናቱ በሌሎች ተቋማትም ላይ የተደረገና በመጠናቀቅ ሂደት ላይ በመሆኑ ከህዝብ ጋር ሆነን ተከታታይ እርምጃዎችን በመውሠድ ሙስና ላይ ድል እንደምንቀዳጅ ተስፋ ሰጥተውናል፡፡ በአናቱም ጠቅላይ ሚንስትር መለስ "የመንግስት ሌቦች" ያሉት እንደነዚህ አይነቶቹን መሆኑን እናስታውስ።

ስለሆነም ከመንግሥት ጎን ሆነን ሙስና ላይ ድል ለመቀዳጀት መዘጋጀት የሁላችንም ፍላጎት ነው፡፡ ለነገሩ የፖለቲካ ልዩነት ምናምን የሚሉቱ ይሁን እንኳ ብንል አሁን ከታሠሩት ውስጥ ሥንቶቹ ይሆኑ ፖለቲከኞቹ? ከመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነት ባሻገር የትኞቹስ ይሆኑ በኢህአዴግ፣ ህውሃት፣ ብአዴን ደኢህዴን ኦህዴድ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ውሣኔ መስጠት የሚያስችል ድርጅታዊ ሥልጣን ያላቸው? ብለን መጠየቅም እኮ እንችላለን፡፡ ግን ህዝብ አያውቀም ብለው እስከዛሬ ከሚቆዝሙቱ ህዝቡ ብዙና የተሻለ ያውቃል ፡፡ መላኩ ፈንታም ሆነ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ በድርጅቱ ውስጥ ከዚህ ግባ የሚባል ስልጣን የሌላቸው ምናልባትም በማዕከላዊ ኮሚቴ ድምፃቸው ይቆጠር ካልሆነ በሥተቀር የእነርሱ ልዩነት ሥርዓቱ ላይ የሚጨምረውም

የሚቀንሠውም ነገር በሌለበት ሁኔታ የፖለቲካ ልዩነት ነው ማለት ለእኔ እና ለተዘረፍነው ሁሉ ፀረ ህዝብ መሆንና የሙሠኞች ተባባሪ መሆን ነው፡፡

ስለሆነም ለእንደዚህ ዓይነት የረከሡ አስተያየቶች መስሚያችን ጥጥ ነው፡፡ በቁማችን ከመበላት ለፀረ ሙስና ትግሉ አስፈላጊውን መስዋዕትነት እንከፍላለን፡፡